ቀን 03 20151

5-6-1/4ጠ/15

13/03/15

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Revenues

በአባሪው ለተገለፁት በሙሉ

ገቢዎች ሚኒስቴር

ጉዳዩ፡- በመመሪያ ቁጥር 176/2014 አፈጻጸም ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች የተሠጠ የህግ ማብራሪያ ይመለከታል

የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች በታክስ አፕሬሽን ዘርፍ አስተባባሪነት ወይይት አድርገው ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ የሚሆን ግብዓት ከተሰባሰበ በኋላ የሚከተለው የህግ አስተያየት ተሰጥቷል።

የንግድ ስራ ሀብትን በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ

በታክስ ሂሳብ መገበያ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀጽ 7 /ተ/ ላይ "የንግድ ሥራ ሀብት ትክክለኛ ዋጋ ያልተገኘለት እንደሆነ የንግድ ስራ ሀብት ዋጋ የመገመት ሥልጣን በህግ ከተሰጠው አካል የተዘጋጀ ትክክለኛ የዋጋ መግለጫ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል።"ይላል። የሚገምተው አካል ማን እንደሆነ በግልጽ ቢቀመጥ እና በምን ሁኔታ ነው ግምት የሚፈቀደው የሚለው ቢብራራ፤ በተጨማሪም ከገቢ ግብር አዋጁ ጋር የሚጋጭ የሚመስል ነገር ስላለው (የገቢ ግብር አዋጁ አንድ የንግድ እቃ የተገዛበትን ቀን፣ ዋጋ፣ መጠን በግልጽ ሊያሳይ የሚችል ማስረጃ መያዝ አለበት) ስለሚል ግልፅ የአሰራር ስርዓት ቢበጅለት።

ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ማብራሪያ

ስለተቀናሽ ወጪዎች የገንዘብ ሚኒስቴር በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 19(1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 መሰረት ለታክስ

ሕጉች ዓላማ በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው የዕቃው፣የንብረቱ፣የአገልግሎቱ ወይም የጥቅሙ

የወቅቱ እና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ መሆን እንዳለበት ስለተደነገገ "የንግድ ሥራ ሀብት ትክክለኛ ዋጋ ያልተገኘለት እንደሆነ የንግድ ስራ ሀብት ዋጋ የመገመትሥልጣን በህግ ከተሰጠው አካል የተዘጋጀ ትክክለኛ የዋጋ መግለጫ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል።" መባሉ የንግድ ሥራ ሀብቱ ትክክለኛ ዋጋ ያልተገኘለት ከሆነ የሀብቱን ትክክለኛ ዋጋ ማወቅ ለታክስ አስተዳደሩ ስለሚያስፈልግ ነው።

በገቢ ግብር አዋጁ ላይ አንድ ግብር ከፋይ የንግድ እቃ የተገዛበትን ቀን ፣ዋጋ፣ መጠን በግልጽ ሊያሳይ የሚችል ማስረጃ መያዝ አለበት ተብሎ መደንገጉ የንግድ ሀብት ወይም ሌላ ሀብት ትክክለኛ ዋጋ መታወቅ ለታክስ አስተዳደሩ የሚያስፈልግ መሆኑን ስሚያመላክት የንግድ ሥራ ሀብቱ ትክክለኛ ዋጋ ካልታወቀ የሀብት ትክክለኛ ዋጋ የመገመትሥልጣን በህግ ከተሰጠው አካል እንዲመጣ ማድረግ የአዋጁን እሳቤ ከማስፈፀም ውጪ ከመመሪያው ጋር የሚጋጭ መሆኑን አያሳይም።መመሪያ እናት ህግን ማለትም አዋጅን ወይም ደንብን ለማስፈፀም የሚዘጋጅ እንጅ በራሱ መብትና ግዴታ የሚመሰርት እንዳልሆነ ይታወቃል። በዚህ መሰረት በታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀጽ 7(1-ተ) ላይ የንግድ ሥራ ሀብት ትክክለኛ ዋጋ ያልተገኘለት የሚለው የንግድ ሥራ ሀብቱ በተለያያ ምክንያት ለምሳሌ ለንግድ ሥራ ሀብቱ የተሰጠው ዋጋ ትክክል ካልሆነ፣ በሰው ሰራሽ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የዋጋ ሰነዶች ከወደሙ ወይም ከጠፉ የንግድ ሥራ ሀብቱ ዋጋ ለታክስ አስተዳደሩ ስለሚያስፈልግ ዋጋው፣ ዋጋ የመገመት ስልጣን በህግ ከተሰጠው አካል ትክክለኛ የዋጋ ግምት ሊቀርብ ይገባል። ስለሆነም በመመሪያው ላይ የተገለፀው "ትክክለኛ ዋጋ ያልተገኘለት..." የሚለው አገላለጽ ዋጋ ያልነበረው የንግድ ሥራ ሀብት ለማለት ሳይሆን ከላይ በተጠቀሱት እና በመሰል ምክንያቶች አሁን ላይ የንግድ ሥራ ሀብቱን ዋጋ የሚገልጹ ሰነዶች የሌሉት የንግድ ሥራ ሀብት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። የሚገምተው አካል ማን ነው? ለተባለው የንብረት አቻ ግምት ለመገመት ይቻል ዘንድ የመገመት ሥልጣን በሚመለከተው አካል ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማለት ነው። ንብረት የመገመት ሥልጣን የተሰጠው አካል የንግድ ሥራ ሀብቱ ትክክለኛ ዋጋ አልተሰጠም ተብሎ በታክሱን በሚያስተዳድረው አካል ከታመነ በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 መሰረት ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ በባለሥልጣኑ የሚወሰን ይሆናል።

ብድርን በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ

በታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀጽ 11 /3/ (ሀ) ላይ ታክስ ከፋዩ ብድሩን የተበደረዉ ከፋይናንስ ተቋም ቢሆንም በቴምብር ቀረጥ ህግ መሰረት የብድር

ዉሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ የተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይገባዋል በማለት ያስቀመጠ ሲሆን በአንቀጽ 11/3/ (ሐ) ላይ የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለ ከሆነ ውሉ በመረጃነት ሊቀርብ ተቀባይነት የሚያገኘው ሁለት አጥፍ ቀረጥ የተከፈለበት ከሆነ ነው በሚል በመመሪያው ተገልጿል። ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከፋይናንስ ተቋም ውጪ ማለትም የግለሰብ ብድር በሚሆንበትም ጊዜ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ግልፅ ስላልሆነ ማብራሪያ ቢሰጥበት፤ እንዲሁም ብድሩ ከፋይናንስ ተቋም ውጪ የተገኘ ሆኖ በውልና ማስረጃ ባይመዘገብና ብድር ስለመሆኑ ማረጋገጥ ካልተቻለ እንደገቢ ተወስዶ መወሰን ይቻላል ወይ? ሁለት አጥፍ የሚለው ቅጣትን ይጨምራል ወይስ ቅጣቱ ሁለት እጥፍ ከሚለው ተጨማሪ ነው? ቴምብር ያልተለጠፈበት ሰነድ ሲቀርብ ቴምብሩ እንዴት ይሰረዝ እና ማን ይሰርዝ? በሚሉት ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ቢሰጥበት።

ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ማብራሪያ

ግብር ከፋዩ ብድሩን የተበደረው ከፋይናንስ ተቋም ቢሆንም በቴምብር ቀረጥ ህግ መሰረት "የብድር ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ የተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባል።" ተብሎ የተገለፀው ከፋይናንስ ተቋማት የብድር ውል ሲከናወን ሰነዶችን የማረጋገጥና የመመዝገብ ስልጣን በህግ በተሰጠው አካል ፊት ባይከናወንም በቴምብር ቀረጥ ህጉ መሰረት በብድር ውሉ ላይ የቴምብር ቀረጥ መከፈል እንዳለበት ለማመላከት የተገለፀ ስለመሆኑ ያሳያል። በታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀጽ 11 /3/ (ለ) ላይ "ግብር ከፋዩ ብድሩን የተበደረው ከፋይናንስ ተቋም ውጪ ከሆነ ሰነዶችን የማረጋገጥና የመመዝገብ ስልጣን በህግ የተሰጠው አካል በብድር ላይ በሚያስከፍለው የቴምብር ቀረጥ መጠን ወይም ልክ የብድር ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ የተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባል።" ተብሎ በማያሻማ ቋንቋ ተገልጿል። ስለሆነም ማንኛውም የብድር ውል (ከባንክም ይሁን ከሌላ ሰው የተገኘ ብድር) በመረጃነት ሊቀርብ የቴምብር ቀረጥ የተከፈለበት መሆን አለበት። በውልና ማስረጃ ባይመዘገብና ብድር ስለመሆኑ ማረጋገጥ ካልተቻለ እንደገቢ ተወስዶ መወሰን ይቻላል ወይ? "ግብር ከፋዩ በብድር ያገኘውን ገንዘብ፤ ገቢ ለማግኘት፤ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል ካላዋለ፤ ባልዋለው ብድር

ልክ የወለድ ወጪ ተቀባይነት ስለማይኖረው በብድር የተገኘው ገንዘብ ለንግድ ሥራው እንደዋለ የሚያሳይ ሰነድ ሊኖር ይገባል።" ተብሎ በመመሪያው የተገለጸው የውል ሰነድ መኖር ወይም ውሉ በውልና ማስረጃ መመዝገብ ለታክስ አስተዳደሩ በቂ አለመሆኑን

ያመላክታል። ነገር ግን ታክስ ከፋዩ "ብድር" ብሎ ያቀረበውን መጠን ብድር ስለመሆኑ ወይም ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውጪ ያገኘው ገንዘብ ስለመሆኑ ሙያው የሚጠይቀውን የፋይናንስ አመዘጋገብ ሥራዓት ተከትሎ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን የታክስ ባለስልጣኑም ይህውን ማረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ ግብር ከፋዩ በገቢነት ያልገለጸውና በባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ፤ ከንግድ ስራ ያልተገኘ ወይም ግብር የማይከፈልበት ገቢ ስለመሆኑ በተገቢው ህጋዊ ማስረጃ በግብር ከፋዩ ካልተረጋገጠ በታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀጽ 23 (4) እና (5) መሰረት በታክስ ህግ መሰረት ግብር ይወሰንበታል።

ሁለት እጥፍ የሚለው ቅጣትን ይጨምራል ወይስ ቅጣቱ ሁለት እጥፍ ከሚለው ተጨማሪ ነው? ቴምብር ያተልጠፈበት ሰነድ ሲቀርብ ቴምብሩ እንዴት ይሰብሰብ እና ማን ይሰብስብ? በሚሉት ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ቢሰጥበት። ተብሎ የተጠየቀውን በተመለከተ ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 10(3) ላይ "በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት (admitted in evidence on payment of two times the amount due) ሊቀርቡ ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከ10 ብር ማነስ የለበትም።" እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10(4) ላይ "ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ንዑስ አንቀጾች (አንቀጽ10(3)ን ጨምሮ) የተወሰነው ቅጣት ተፈጻሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሰረት ከመከሰስ አያድንም።" ተብሎ ተደንግጓል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው "ሁለት እጥፍ" ማለትም መከፈል የነበረበት መጠን "መ" ቢሆን የቴምብር ቀረጥ ያልከፈለ ከሆነ ውሉ በመረጃነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚያገኘው 2መ ወይም (መ+መ) ቀረጥ የተከፈለበት ከሆነ ሲሆን ከሁለቱ "መ"ዎች አንደኛው "መ" ቅጣት መሆኑን ያሳያል። ስለሆነም "ሁለት እጥፍ" የሚለው ቅጣትን ስለሚጨምር በታክስ አስተዳደር ህጉ መሰረት ተጨማሪ ቅጣት አያስፈልግም።

በተጨማሪም የብድር ውል በቴምብር ቀረጥ አዋጅ አንቀጽ 2(2) ለማገቻ (ቦንድ) በተሰጠው ትርጉም ውስጥ እንዲካተት ተደርጎ ትርጉም ስለተሰጠው በብድር ውል ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በቴምብር ቀረጥ ታሪፍ ሰንጠረዥ ተ.ቁ 4 መሠረት የብድሩን ዋጋ 1% ይሆናል። በዚሁ መሠረት ተቀባይነት ያላገኘ የብድር ውል ተቀባይነት ለማግኘት በብድሩ ዋጋ ላይ 2% የቴምብር ቀረጥ ሊከፈል ይገባል። ስለሆነም ያልተመዘገበ እና ሰነዱ

ተፈፈመበት ጊዜ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበት የብድር ውል ተቀባይነት ለማግኘት በብድሩ ዋጋ ላይ 2% ቀረጥ ሲከፈልበት ብቻ ተቀባይነት ማግኘት የሚችል

ስለመሆኑ የተገለፀ ስለሆነ በዚሁ መሰረት መፈፀም አለበት።

ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1990 በፌደራል ታክስ አስተዳር አዋጅ መሰረት የሚተዳደር ስለሆነ ወለድን በተመለከተ የታክስ አስተዳር አዋጁ ተፈጻሚ ይሆናል።

ስለሆንም ማንኛውም ታክስ ለመሰብሰብ የታክስ ባለስልጣኑ የሚከተላቸው ህግና ሥራዓቶች ተፈጻሚ ሊሆኑ ይገባል። ለምሳሌ የውሳኔ ማስታወቂያ ሊሰጥ ይገባል። ማን ይስራው? ለሚለው መዋቅራዊ ጥያቅ ስለሆነ ባለው አደረጃጀት መሰረት ኦፕሬሽናል ሥራ መሆኑ ታውቆ በዚሁ አግባብ ሊስተናገድ ይገባል።

መሸጋገሪያ ድንጋጌን በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ

በታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 አንቀጽ30 (1) ላይ ውሳኔ አግኝቶ በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ በዚህ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው ለምን አስፈለገ? ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ተመልሶ በዚህ መመሪያ ማስተናገዱ ተገቢነትስ አለው ወይ? ይፈጸም ከተባለስ በምን በምን ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ግልጽ ቢደረግ ፣ በታክስ ይግባኝና ፍርድ ቤት ክርክር ያሉትስ ለምን በዚህ እንዲታዩ አልተፈቀደም? ይግባኝ በመሄዳቸዉ ብቻ በመመሪያዉ እንዳይስተናገዱ ማድረጉ በታክስ ከፋዮች መካከል ኢፍትሃዊነት የሚያመጣ እና የይግባኝ መብታቸውን እንዳይጠቀሙ በዉጤት ደረጃ የሚከለክል አይሆንም ወይ በሚለው ላይ አስተያየት ቢሰጥበት ተብሎ በተጠየቀው ላይ እንደሚከተለው ማብራሪያ ተሰጥቶበታል።

ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ማብራሪያ

በታክስ ሂሳብ አያያዝ መመሪያ አንቀጽ 30 ላይ "ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ተጀምሮ በታክስ ባለስልጣኑ ውሳኔ ያላገኘ ወይም ውሳኔ አግኝቶ በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ (ይግባኝ የተባለበትን ሳይጨምር) በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛል" ተብሎ የተደነገገውን በተመለከተ መመሪያው ሲዘጋጅ ተፈጻሚ እንዲሆን የታሰበው በሶስት ጉዳዮች ላይ ነው። እነሱም:-

1. መመሪያው ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት በነባሩ መመሪያ መሰረት ተጀምረው ፍጻሜ ባላገኙ ነው። ይህም ማለት በነባሩ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር

152/2011 መሰረት እየተከናወኑ የነበሩ ጉዳዮች አዲሱ የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ፍጻሜያቸውን የሚያገኙት በአዲሱ መመሪያ መሰረት ነው።

2. ውሳኔ አግኝቶ በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ ፍጻሜ የሚያገኘው በታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ነው። ነገር ግን ይህ አዲሱ መመሪያ ለሁሉም ውሳኔ አግኝተው በሂደት ላሉ ጉዳዮች ተፈጻሚ የሚሆን አይደለም። በመመሪያው እንደተጠቀሰው ውሳኔ አግኝቶ በይግባይኝ ላይ ያለ ጉዳይ ፍጻሜ የሚያገኘው ይግባኙን ተቀብሎ እያስተናገደ ባለው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ፍርድ ቤት ነው። ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ፍርድ ቤት ገለልተኛ አካላት እንደመሆናቸው የሚሰጡት ውሳኔ የተከራካሪ ወገኖች ፍትህ መሰረት ተደርጎ የሚሰጥ ወሳኔ እንደመሆኑ የዚህ ውሳኔ አፈጻጸም በሌላ አካል በሚወጣ መመሪያ የሚስተጓጎል መሆን የለበትም።

ስለሆነም መመሪያው ሲዘጋጅ በነበረው አሳቤ መሰረት ውሳኔ አግኝቶ በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ ማለት ጉዳዩ ምንም እንኳ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ቢሆንም፣ ይህ ውሳኔ ያገኘው ጉዳይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ፍጻሜ ያላገኘ መሆኑን ያሳያል። ውሳኔ ባገኘው ጉዳይ ላይ ግብር ከፋዩ ይግባኝ ያቀረበበት ወይም በውሳኔው መሰረት ፍጻሜ ያገኘ ከሆነ የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ተፈጻሚ አይሆንም። ነገር ግን ውሳኔ ባገኘው ጉዳይ ላይ ግብር ከፋዩ ይግባኝ ያላቀረበበት እና በውሳኔው መሰረት ፍጻሜ ያላገኘ ከሆነ የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ተፈጻሚ ይሆናል።

በአጠቃላይ የታክስ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/2014 ተፈጻሚ የሚሆነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 30 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ አንቀጽ 31 መሰረት ከ29/08/2014 ዓ.ም ጀምሮ ነው።

ከሰላምታ ጋር

አዳነ አስፋው ከበደ
የሀገ አገልግሎት
ጀነራሉቶራት ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ አፕሬሽን ዘርፍ
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ